# ድምጸ ብርሃን

ብርሃን Berhan Bank

እንደ ስማችን ብርሃን ነው ሥራችን!

ቁ.1/ ግንቦት /2014 ዓ.ም

## | አዲስ ምዕራፍ-አዲስ አመራር



ብርሃን ባንክ ከጥር 24/2014 ዓ.ም ጀምሮ አቶ ግሩም ፀጋዬን አዲስ ፕሬዝዳንት አድርጎ ሾሟል፡፡ አቶ ግሩም ፀጋዬ ከፍተኛ የባንክ ስራ ልምድ ያላቸው ሲሆን የባንኩን ውጤታማነት ከፍ ለማድረግ የላቀ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክቱ ይጠበቃል፡፡

# ርዕሰ አንቀጽ

## ብርሃን ባንክ በለውጥ ጎዳና

ይህች የመጀመሪያ ዕትም የውስጥ መጽሔታችን ነች። ዓላማዋ የብርሃን ባንክ ሰራተኞች የመረጃ መለዋወጫ እና ማንቂያ መድረክ እንድትሆን ነው። የባንኩ ሰራተኞች ስለ ባንካቸው እንዲሁም ስለ ኢንደስትሪው ጠቃሚ መረጃ እንዲኖራቸው ትረዳለች ብለን እናምናለን።

ተግባቦት (Communication) ሁነኛ የውጤታማነት ግብዓት ነው። በቂ የሆነ ተግባቦት በሌለበት ጊዜ ግራ መጋባት ይነግሳል። ስለዚህ ይህች መጽ ሄት የውስጥ ተግባቦትን (Internal communication) ታሳልጣለች ብለን እናምናለን። ደግሞም የለውጥ ቀስቃሽ ትሆናለች።

ተቋም መሰረታዊ ለውጥ ለማድረግ የሚገደድባቸው ጊዜያት ይኖራሉ። ለብርሃን ባንክ አሁን የለውጥ ጊዜ ነው ባንኩ የ5 አመት መሪ እቅድ እያዘጋጀ ሲሆን ከፊታችን ባለው አዲስ የበጀት አመት ተግባራዊ ይሆናል። የባንኩ ፕሬዝዳንት ለውጡ ውጤት እንዲያመጣ ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል። ምንም እንኳን ለውጥ ቀላል ባይሆንም የብርሃን ባንክ ሰራተኞች ግን ለውጥን በመቀበል፤ በማገዝ እና በመተግበር ባንካቸውን ወደ ትልቅነት ይገፉታል ብለን እናምናለን።



## ማውጫ


ርዕስ አንቀጽ 2
ዜና ብርሃን 2
ደንበኛህን እወቅ 3
ኢኮኖሚ 6
እናስተዋውቅዎ 6
ተሞክሮ 8
ቅምሻ 7
ስለ ስኩል ፔይ 1


## ኤዲቶሪያል ቦርድ


አቶ ሰለሞን አሰፋ ሰብሳቢ
አቶ ወሰን አለምዬ ም/ሰብሳቢ
አቶ ግሩም ታሪኩ ጸሀፊ
አቶ አሰፋ አባል
አቶ ዋለ አባል


## የዝግጅት ክፍል


አቶ ግሩም ታሪኩ አስተባባሪ
ወ/ሮ እምነት ተሸመ ዋ/አዘጋጅ
ወ/ሮ ቤተልሄም አሻግሬ ረ/አዘጋጅ
አቶ ዳግማዊ አዘጋጅ

# ዜና ብርሃን

## 3ኛ ሩብ አመት አፈጻጸም እና ስትራቴጂክ እቅድ ውይይት



ብርሃን ባንክ የ3ኛ ሩብ አመት አፈጻጸም እና ስትራቴጂክ እቅድ ላይ ውይይት አካሂዷል፡፡

ውይይቱ የባንኩ ፕሬዝዳንት አቶ ግሩም ጸጋዬ፤ የባንኩ ከፍተኛ የስራ አመራሮች እና የቅርንጫፍ ስራአስኪያጆች በተገኙበት በተሳካ ሁኔታ ተካሂዷል፡፡

በዕለቱም የ3ኛ ሩብ አመት አፈጻጸም እና ስትራቴጂክ እቅዱ ለተሳታፊዎች ቀርቦ ውይይት የተደረገበት ሲሆን ከፕሬዝዳንቱ ጋር የትውውቅ ፕሮግራምም ተከናውኗል፡፡

ባንኩ ስትራቴጂክ እቅዱን እ.ኤ.አ ከጃኑዋሪ 1 2022 ጀምሮ ለውጭ አማካሪ ድርጅት ለሆነው ለኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት እንዲያዘጋጅ በመስጠት በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

አሁን ላይ የራዕይ ተልዕኮና እሴት እና ቀረጻ ስራ እየተከናወነ ሲሆን በቀጣይም፤ ስትራቴጂዎችን እና ራዕይ ተልዕኮና እሴት መርጦ የማጽደቅ፣ የትግበራ ዕቀድ የማዘጋጀት፣ የአንድ ዓመት ኦፕሬሽናል ዕቅድ የማዘጋጀት; የስልታዎ ዕቅድ ክትትልና ቁጥጥር መመሪያን የማዘጋጀትና የመጨረሻውን ዶክመንት አዘጋጅቶ የማስረከብ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

## በብርሃን ባንክ የተደረገ ድጋፍ



ብርሃን ባንክ በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 አስተዳደር ለተፈናቀሉ ወገኖች ማቋቋሚያ የሚሆን የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ላይ ድጋፍ አደረገ፡፡ ድጋፉ ለተፈናቀሉ ወገኖች ምግብና የምግብ ግብአት ሲሆን ባንኩ ማህበራዊ ሃላፊነቱን በመወጣት አስፈላጊውን ድጋፍ አድርጓል፡፡

በተመሳሳይም ባንኩ አረጋዊያንን ጨምሮ ድጋፍ የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎችን በመደገፍ እየሰራ ለሚገኘው ባዩሽ ኮልፌ የበጎ አድራጎት ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

## የዲጂታል ግብር

ብርሃን ባንክ ግብር ከፋዮች የሚጠበቅባቸውን ግብር ባሉበት ሆነው በዲጂታል ቻናሎች የሚከፍሉበትን አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

አዳዲስ አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ፤ በተደራጀና ለደንበኞች ምቹ በሆነ መልኩ በማቅረብ የሚታወቀው ባንኩ ይህን አገልግሎት ከጀመሩ ጥቂት ባንኮች ዉስጥ አንዱ ለመሆን ችሏል፡፡

በዚህም ግብር ከፋዮች ወደ ግብር ክፍያ ማዕከል መሄድ ሳይጠበቅባቸው ባሉበት ሆነው በዲጂታል ቻናሎች 24/7፤ በሞባይል ወይም ኢንተርኔት ባንኪንግ መክፈል የሚያስችላቸው ነው፡፡

ባንኩ የንግዱ ህብረተሰብ በመዘግየት ምክኒያት ከሚመጣበት ቅጣት እራሱን ታድጎ ያለምንም መንገላታት በባንኩ በተዘረጉ አማራጮች ግብሩን የሚከፍልበት ዘመናዊ የዲጂታል ግብር አከፋፈል አገልግሎትን ነው ያስጀመረው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ግብር ከፋዮች አቅራቢያቸዉ በሚገኝ የባንኩ ቅርንጫፎች በመቅረብ ከሂሳባቸዉ ገንዘብ በማስተላለፍ ወይም በጥሬ ገንዘብ ግብር የሚከፈልበት አማራጭም እንዳለው አስታውቋል፡፡




## ከብርሃን ባንክ ሂሳብ ወደ ሌላ ባንክ ገንዘብ ማስተላለፍ

ሞባይል ባንኪንግን በመጠቀም ከብርሃን ባንክ ሂሳብ ወደ ሌሎች ባንኮች ሂሳብ ገንዘብ የማስተላለፍ አገልግሎት ተጀምሯል፡፡

ይህ አገልግሎት ከሌሎች ባንኮችም ገንዘብ መቀበልን የሚያካትት ሲሆን አንድን የብርሃን ባንክ ደንበኛ ከሂሳቡ ላይ ወደ ሌላ ባንክ የራሱ ወይም የሌላ ሰዉ ሂሳብ ገንዘብ ማስተላለፍም ሆነ መቀበል የሚያስችለዉ አሰራር መሆኑን ባንኩ አስታውቋል፡፡

# ደንበኛህን እወቅ




የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እ.አ.አ ኦገስት 27 ቀን 2021 በቁጥር V/G/FIS/016/2021 የሂሳብ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች እንዲሁም ከእንቅስቃሴ ገደብ ጋር የተያያዘ መመሪያ አውጥቷል። በመሆኑም በሂሳብ ላይ የተመሰረቱ እንቅስቃሴዎችን ለማካሄድ ከወጣው እና ከገንዘብ እንቅስቃሴ ገደብ ጋር ተያይዞ ከወጡት መመሪያዎች ውስጥ:-

| የብሔራዊ መታወቂያ እስኪዘጋጅ ደረስ ማንኛውም ደንበኛ በአንድ ባንክ ውስጥ አንድ ልዩ ቁጥር (የደንበኛ ቁጥር) ሊኖረው እንደሚገባ ያዝዛል።

| ባንኮች ደንበኞቻቸውን በደንብ እንዲያውቁ ወይም ስለደንበኞቻቸው የተሟላ መረጃ እንዲኖራቸው እንዲሁም ከሂሳብ ወደ ሂሳብ የሚደረጉ የገንዘብ ዝውውሮች ላይ ገደብ የተጣለ ሲሆን መመሪያውም ተገባራዊ የሚደረገው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ወስጥ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል።

| መመሪያው አነስተኛ ገቢ ያላቸውን እና መታወቂያ ማቅረብ የማይችሉ ደንበኞችን በባዮሜትሪክስ የጣት አሻራ ፣ በደንበኛው ፊረማ እና በፎቶግራፍ ብቻ በመታገዝ (ያለ መታወቂያ) ሂሳብ መክፈት የሚችሉ ይሆናል።

| መመሪያው ባንኮች የማይታወቅ ማንነት ባላቸው ግለሰቦች ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ስም ላላቸው ደንበኞች ሂሳብ መክፈት እንደማይችሉ ይደነግጋል

| የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው የደንበኛ መረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ(የሂሳብ መክፈቻ ቅጽ) መሰረት መረጃቸውን ያላሟሉ ደንበኞች በስድስት ወራት ወስጥ እንዲያሟሉ ሲደነግግ ደንበኞቹን ማግኘት እንዲሁም መረጃቸውን ማሟላት ካልተቻለ ግን በስፋት በሚሰራጩ የህትመት ወይም በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ላይ ጥሪ ተደርጎ እንዲያሟሉ ይደረጋል ካልሆን ግን ለጊዜው ደንበኞቹ መረጃዎቻቸውን እስኪያሟሉ ደረስ ሂሳቡ እንዳይንቀሳቀስ ይደረጋል።

| በሃገሪቱ ያሉ ጠቅላላ ባንኮች ተመሳሳይ ቅጾችን (የሂሳብ መክፈቻ፤ የገቢ፤ የወጪ ማዘዣ እና የመሳሰሉ) እንዲጠቀሙ መመሪያው ያዛል አፈጻጸሙም መመሪያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ተግባራዊ ይደረጋል

| በባንኩ ውስጥ ሂሳብ የሌለው ደንበኛ ወደ ሶስተኛ ወገን ሂሳብ ጥሬ ገንዘብ ገቢ ማድረግ እንደማይችል እንዲሁም ሐዋላ መላክ እንደማይችል ይደነግጋል

| ድርጅቶች ጥሬ ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ ማድረግ ሲፈልጉ ሰራተኞቻቸውን በደብዳቤ በመወከል ገቢ ማድረግ ይችላሉ።

# ስለ ስኩል ፔይ

"ስኩልፔይ አገልግሎት ከተለመደው በጥሬ ገንዘብ ከሚሰበሰበው የመደበኛ ት/ቤት፣ የኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ክፍያ ፍጹም በተለየ መልኩ ተማሪዎች ወይም ወላጆች ት/ቤት መሄድ ሳያስፈልጋቸው ካሉበት ቦታ ሆነው በማንኛውም ሰዓት የተማሪ ኮድ በመጠቀም ክፍያ የሚፈጸምበት ዘመናዊ አሠራር ነው።"

ወላጆች ወይም ተማሪዎች የስኩል ፔይ አገልግሎት ለመጠቀም እንዲችሉ ተማሪዎች የሚማሩበት ት/ቤት ከባንካችን ጋር በዌብፖርታል መገናኘት አለበት። ከዚያም በኃላ ስኩል ፔይ ሲስተም ላይ እያንዳንዱ ተማሪ ሲመዘገብ ልዩ ኮድ ይሰጠዋል ይህንኑ ልዩ ኮድ በመጠቀም ወላጅ ወይም ተማሪ የትምህርት ክፍያ በሞባይል ባንኪንግ ወይም በኢንተርኔት ባንኪንግ ወይም አቅራቢያ በሚገኘው የብርሃን ባንክ ቅርንጫፍ በኩል በቀላሉ መክፈል ይችላሉ።

ተማሪዎች ወይም ወላጆች የስኩል ፔይ አገልግሎት በመጠቀማቸው ጊዜና ወጪአቸውን ከመቆጠባቸውም ባሻገር በማንኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ ሆነው የትምህርት ክፍያ ለመፈፀም ያስችላቸዋል።"

ባንካችን የስኩል ፔይ አገልግሎት በመጀመሩ በርካታ ደንበኞች ከማግኘቱም በላይ ከፍ ያለ ተቀማጭ ገንዘብ እንዲያገኝ አስችሎታል።፡

"የስኩልፔይ ዘመናዊ ክፍያ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከዛሬ ድረስ 240 የግል ት/ቤቶች ከባንካችን ጋር እንዲሰሩ ከፍተኛ እድል ፈጥሯል።" ይህንኑ የስኩል ፔይ አገልግሎት የደንበኞቻችንን ፍላጐት ማዕከል በማድረግ በየጊዜው እንዲሻሻል በርካታ መደበኛ ት/ቤቶች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ለመድረስ ከባንካችን ቅርንጫፎች ጋር በመቀናጀት አዳዲስ ት/ቤቶችን ወደ ባንካችን ለማምጣት እቅድ አውጥተን በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን።



# |ኢኮኖሚ




እንደ የአለም አቀፍ ገንዘብ ተቋም (አይ.ኤም.ኤፍ) ዘገባ የአለም ኢኮኖሚ ባሳለፍነዉ እ.ኤ.አ 2021 የ5.9 በመቶ እድገት ያስመዘገበ ሲሆን ከሰሀራ በታች ያሉት ሀገራት ድርሻ 3.5 በመቶ እድገት ነዉ። እድገቱ የተቀዛቀዘበት ምክኒያት በዋናነት የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ተከትሎ የተከሰተ የምርት መቀዛቀዝ ተጠቃሽ ነዉ። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባሳለፍነው እ.ኤ.አ 2021 የ6.3 በመቶ እድገት ያስመዘገበ ሲሆን ከዚህም ዉስጥ የግብርናዉ 5.3%፤ የማኑፋክቸር 7.3% እና የሰርቪስ ድርሻ 6.3% በቅደም ተከተል ነው።

እ.ኤ.አ በ2022 የአለም ኢኮኖሚ በ4.4 በመቶ እድገት እንደሚያሳይ የሚጠበቅ ሲሆን የሰሀራ በታች አገሮች ደግሞ በ3.8 በመቶ እድገት ሊያስመዘግቡ እንደሚችል ይጠበቃል። ይሁንና **የአለም አቀፍ ገንዘብ ተቋም (አይ.ኤም.ኤፍ) ም ሆነ ሃገር በቀል ተቋማት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በ2022 ስለሚኖረው ምጣኔ እድገት ይህ ነው የሚባል ትንበያ ለማስቀመጥ ቢቸገሩም መንግስት ጦርነቱን ለመገባደድ እና የልማት ድርጅቶችን ወደግል ለማዞር በያዘዉ ተስፋሰጭ እቅድ ምክኒያት ኢኮኖሚው ካለፈው የመነቃቃት ተስፋ ተጥሎበታል።**

በሌላ በኩል እ.ኤ.አ በጥር 2022 የተመዘገበዉ አመታዊ የዋጋ ግሽበት 34.5 በመቶ ሲሆን ከህዳር ወር 35.1 በመቶ ጋር ሲነፃፀር የ1.7 በመቶ ቅናሽ ያሳየ ቢሆንም ዋጋን ለማረጋጋት ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ በመሆኑ የብሄራዊ ባንክ የብድር አሰጣጥን አስመልክቶ ያወጣዉ መመሪያ የራሱ ድርሻ ሊኖረዉ እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን የምርት አቅርቦትን በማሳለጥና ምርታማነትን በማሳደግ በተለይ የምግብ ነክ ሸቀጦች ላይ ሊሰራ እንደሚገባ መረዳት አያዳግትም፤

የኢትዮጵያ የግል ባንኮች በአጠቃላይ በተቀማጭ ሂሳብና በብድር ክምችት እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 2021 ድረስ የ40% እንዲሁም በብድር ክምችት የ37% አመታዊ ጭማሪ ወይም እድገት በማስመዝገብ የብር 626 ቢሊዮን ተቀማጭ ገንዘብና የብድር 507 ቢሊዮን የብድር መጠን ላይ ደርሰዋል። የጠቅላላ ሀብት መጠንም የ40% አመታዊ እድገት በማሳየት ብር 791 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ጠቅላላ የካፒታል መጠንም የ30% ጭማሪ በማሳየት ብር 54.8 ቢሊየን ደርሷል። አጠቃላይ ትርፍም የ30% አመታዊ እድገት በማሳየት ብር 27.1 ቢሊየን የደረሰ ሲሆን የቅርንጫፎች ብዛትም የ15% ጭማሪ በማሳየት 5027 ደርሷል።

Cephus Capital 2022, Page 4
IMF January, 2022
Cephus Capital 2022, page 31

**“የአለም አቀፍ ገንዘብ ተቋም (አይ.ኤም.ኤፍ) ም ሆነ ሃገር በቀል ተቋማት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በ2022 ስለሚኖረው ምጣኔ እድገት ይህ ነው የሚባል ትንበያ ለማስቀመጥ ቢቸገሩም መንግስት ጦርነቱን ለመገባደድ እና የልማት ድርጅቶችን ወደግል ለማዞር በያዘዉ ተስፋሰጭ እቅድ ምክኒያት ኢኮኖሚው ካለፈው የመነቃቃት ተስፋ ተጥሎበታል።”**




# SCH Pay

ስኩል ፔይ የኮሌጅ ወይም የዩኒቨርሲቲ የትምህርት ክፍያ ፍፁም በተለየ መልኩ ተማሪዎች ወይም ወላጆች ትምህርት ቤት መሄድ ሳያስፈልጋቸው ካሉበት ቦታ ሆነው ለመክፈል የሚያስችል ዘመናዊ አሰራር ነው

ለበለጠ መረጃ +251 11 663 0127
+251 11 618 5732
ይደውሉ

www.berhanbanksc.com

ብርሃን
Berhan Bank

Tel +251 11 663 0127 / +251 11 618 5732
+251 11 662 9568
Fax +251 11 662 3431 Swift BERHETAA
E-mail info@berhanbanksc.com www.berhanbanksc.com
P.O.Box 387 Code 1110, Addis Ababa, Ethiopia




## Berhan Mobile Banking

Dial *881# or download and install Berhan Mobile Banking app from Google Playstore and take advantage of easy and comfortable banking services.

GET IT ON Google Play

berhanbanksc

www.berhanbanksc.com

Berhan Bank

ለበለጠ መረጃ
+251 11 663 0127
+251 11 618 5732 ይደውሉ

Tel +251 11 663 0127 / +251 11 618 5732
+251 11 650 7425
Fax +251 11 662 3431 Swift BERHETAA
E-mail info@berhanbanksc.com www.berhanbanksc.com
P.O.Box 387 Code 1110, Addis Ababa, Ethiopia

# እናስተዋውቅዎ

ብርሃን ባንክ ከመሰረተበት ጊዜ አንስቶ በቴክኖሎጂና ወቅቱ በሚፈልገው ዘመናዊ የዲጂታል አገልግሎቶች አሰራሩን በማዘመን እና በማስፋት በደንበኞች ዘንድ ተደራሽ እየሆነ ይገኛል፡፡ ባንኩ እየሰራባቸው ስለሚገኙ ዘመናዊ የባንክ አሰራሮች በቂ መረጃ እንዲሰጡን በባንካችን ዲጂታል ፋይናንሺያል ሰርቪስስ ዳይሬክተር የሆኑትን አቶ ፈዬራ ኢጄታ የዚህ አምድ የመጀመሪያ እንግዳ አድርገን ጋብዘናል፡፡ መልካም ንባብ!

**ድምጸ ብርሃን፡** በቅድሚያ ከተጣበበ ጊዜዎ ላይ ይህንን ቃለመጠይቅ ለማድረግ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ እናመሰግናለን፡፡

**አቶ ፈዬራ፡** እኔም አመሰግናለው

**ድምጸ ብርሃን፡** እራስዎትን ቢያስተዋውቁን እና ወደ ብርሃን ባንክ የመጡበትን አጋጣሚ ቢገልጹልን?

**አቶ ፈዬራ፡** ፈዬራ ኤጄታ እባላለሁ፡፡ በባንክ ኢንዱስትሪ ውስጥ ከ20 ዓመት በላይ የሥራ ልምድ አለኝ፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የመጀመሪያዎቹ ስምንት ኤ.ቲ.ኤም ሲተከሉ በኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅነት አገልግያለሁ እንዲሁም በተለያዩ ኃላፊነቶች ለባንኩ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት የመጡትን Earnest and Young እና BOSI የCounter party ማስተባበሪያ ቢሮ መርቻለሁ፡፡

በተጨማሪም በዲስትሪክት ስራ አስኪያጅነት አገልግያለሁ፡፡ በኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ለማቋቋም በተደረገው እንቅስቃሴና የብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ ዶክመንቶችን በማዘጋጀትና የAlternative Banking ኘሮጀክቱ በሥራ አስኪያጅነት አገልግያለሁ፡፡ በኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክም የስትራተጂና ለውጥ አስተዳደር በቺፍ ኦፊሰርነት አገልግያለሁ፡፡ እ.ኤ.አ ዲሴምበር 1 2018 ወደ ብርሃን ባንክም የመጣሁት ያለኝ ሥራ ልምድ በዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት ሥራ ላይ ለማካፈል ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓትም በብርሃን ባንክ ዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት ላይ በዳይሬክተርነት ተመድቤ በማገልገል ላይ እገኛለሁ፡፡

**ድምጸ ብርሃን፡** ብርሃን ባንክ እየሰጣቸው የሚገኙት ዋና ዋና አገልግሎቶች ምንምን ናቸው?

**አቶ ፈዬራ፡ ብርሃን ባንክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዲጂታል ባንኪንግ ያስጀመረው /በኤ.ቲ.ኤምና በፖስ/ አማካይነት የሚሰራ የካርድ ባንኪንግ አገልግሎት ነው፡፡** በአሁኑ ግዜ ባንካችን በርካታ የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎቶችን ሥራ ላይ በማዋል ደንበኞቻችንን በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ የምንሰጣቸው የዲጂታል ባንኪንግ ዋና ዋና አገልግሎቶች፤ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የቪዛ እና ማስተር ካርድ ባንኪንግ፤ ሞባይል ባንኪንግ፤ ኢንተርኔት ባንኪንግ፤ በኢትዮጵያ አየር መንገድ እና በGUZOGO Platform የዲጂታል አየር ቲኬት ክፍያ አገልግሎት፤ በSchoolPay System የት/ቤት ክፍያዎች፤ የዲጂታል ግብር ክፍያ አገልግሎት፤ የስልክ ቅድሚያና ድህረ ክፍያ የሞባይል ክፍያ አገልግሎት፤ የቴሌ ብር እንዲሁም የኢ-ኮሜርስ አገልግሎት ናቸው፡፡

**ድምጸ ብርሃን፡** ባንኩ የተለያየ አገልግሎትን ማስተዋወቅ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አገልግሎቱ ለባንኩ እና ለህብረተሰቡ ያስገኘው ጠቀሜታ ምንድነው ይላሉ?

**አቶ ፈዬራ፡** የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት ለባንካችን የሚሰጠው ጠቀሜታ እጅግ ብዙ ነው፡፡ በዋናነት የወደፊትም የባንካችን የቢዝነስ እድገት ያለው በደጂታል ባንኪንግ አገልግሎት ዙሪያ ነው ብዬ አምናለው፡፡ ባንካችን ለደንበኞች በቅርንጫፍ ውስጥ በሰው ኃይል ተጠቅሞ የሚሰጠው አገልግሎት ደንበኛው በራሱ ጊዜ በማንኛውም ሰዓት ከየትኛውም ቦታ 24/7 የባንክ አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ ሠራተኛውን ለሌላ የቢዝነስና የማርኬቲንግ ሥራ ማሰማራት ይችላል፡፡ የባንካችን የኦኘሬሽናል ወጪውንም ይቀንሳል፤ እንዲሁም ከዲጂታል የባንክ አገልግሎት ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡ በተጨማሪም የደንበኞች አገልግሎት የተቀላጠፈ እንዲሆን ያግዛል፡፡ ይህ አገልግሎት መኖሩ ነባር ደንበኞች ወደ ሌላ ባንክ እንዳይሄዱ ከማድረጉም በላይ ሌሎች አዳዲስ ደንበኞች ወደ ባንካችን እንዲመጡ የሚያስችል ነው፡፡ ዲጂታል ባንኪንግ ለባንካችን ከሚሰጠው ጥቅም ባሻገር የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚ ያልሆኑ የማህበረሰብ ክፍል በደጂታል ባንኪንግ ተደራሽ ይሆናሉ፡፡ ነባር ደንበኞችም ቀላል፣ ቀልጣፋና ምቹ የሆነ የባንክ አገልግሎት 24/7 ሰዓት እንዲያገኙ ያስችላል፡፡ System የት/ቤት ክፍያዎች፤ የዲጂታል ግብር ክፍያ አገልግሎት፤ የስልክ ቅድሚያና ድህረ ክፍያ የሞባይል ክፍያ አገልግሎት፤ የቴሌ ብር እንዲሁም የኢ-ኮሜርስ አገልግሎት ናቸው፡፡

**ድምጸ ብርሃን፡** ባንኩ የተለያየ አገልግሎትን ማስተዋወቅ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አገልግሎቱ ለባንኩ እና ለህብረተሰቡ ያስገኘው ጠቀሜታ ምንድነው ይላሉ?

**አቶ ፈዬራ፡** የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት ለባንካችን የሚሰጠው ጠቀሜታ እጅግ ብዙ ነው፡፡ በዋናነት የወደፊትም የባንካችን የቢዝነስ ...........ወደ ገጽ 10 ዞሯል

**“ብርሃን ባንክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዲጂታል ባንኪንግ ያስጀመረው /በኤ.ቲ.ኤምና በፖስ/ አማካይነት የሚሰራ የካርድ ባንኪንግ አገልግሎት ነው፡፡”**



# ቅምሻ

ገንዘብን እና ሌሎች ውድ እቃዎችን በጥብቅ በታዎች ማስቀመጥ እንደዛሬ ባንኮች ባልነበሩበት ጊዜም ይተገበር ነበር። በወቅቱ እነዚህ የተጠበቁ በታዎች ቤተመቅደሶች ነበሩ። ለምሳሌ በቀድሞዋ የአቴና ግዛት ሰዎች ተቀማጭ ገንዘቦቻቸውን አክሮፖሊስ በተሰኘችው እና በተራራማ ቦታ ላይ ባለች አነስተኛ ከተማ ውስጥ ባለ ቤተመቅደስ ውስጥ ያስቀምጡ የነበረ ሲሆን በመካከለኛው ዘመን የነበሩ አውሮፓውያን ገንዘቦቻቸውን በገዳማት ውስጥ ያስቀምጡ ነበር።

ባንክ የተሰኘው ቃል የመጣው ከጣልያንኛ ቋንቋ ሲሆን መሰረቱም ባንኮ (banco) አግዳሚ ወንበር ወይም ጠረጴዛ ከሚለው ቃል ጋር ተመሳስሎሽ ያለው ነው። **"ባንኮ በጊዜው በቬኒስ ሪፐብሊክ የምንዛሪ አገልግሎት እና ከፍተኛ ወለድ የሚታሰብበት አራጣ ያበድሩ የነበሩ ሰዎች ገንዘቦቻቸውን እና ተያያዥ ሰነዶችን የሚያስቀምጡባቸው የቁሶች መጠሪያ ነበር።"** አይሁዳውያን ኪሳራ ቢገጥማቸው እና በገቡት ውል መሰረት እዳቸውን መክፈል ሲሳናቸው በእነዚህ ቁሶች አናታቸውን ተመትተው ቁሶቹ ይሰበራሉ በዚህም ምክንያት ከጣልያንኛው ሃረግ ‹banco rotto› ሰባራ አግዳሚ/ወንበር (broken bench") ዘመናዊው ቃል ‹bankrupt› በእኛ ቋንቋ ኪሳራ የሚለው ቃል እንደተወለደ ይነገራል።

> "ባንኮ በጊዜው በቬኒስ ሪፐብሊክ የምንዛሪ አገልግሎት እና ከፍተኛ ወለድ የሚታሰብበት አራጣ ያበድሩ የነበሩ ሰዎች ገንዘቦቻቸውን እና ተያያዥ ሰነዶችን የሚያስቀምጡባቸው የቁሶች መጠሪያ ነበር።"

በመካከለኛው የአውሮፓውያን ዘመን የሮማ ጳጳሳት ወለድ የሚታሰብበት የጥሬ ገንዘብ ብድርን ማበደር የከፋ ሃጥያት እንደሆነ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው። ስለዚህም እ.ኤ.አ 1179 አቡነ አሌክሳንደር 3ኛው አራጣ አበዳሪዎች የከፋ ሃጢያተኞች ተብለው ስለተወገዙ ከማናቸውም የማሕበራዊ አኗኗር የተገለሉ እንዲሆኑ እና ሰዎች ከእነዚህ አራጣ አበዳሪዎች ማናቸውንም ዓይነት ማህበራዊ ኑሮን እነዳይመሰረቱ እንዲሁም እንዲርቋቸው አወጁ። በተጨማሪም ጳጳሱ "bankers" ወይም የወቅቱን የባንክ አገልግሎት ሰጪዎች ሲሞቱ አስከሬኖቻቸው ቅዱስ በታዎች ተብለው በተለዩ በታዎች እንዳይቀበሩ ይልቁንም በወቅቱ ራሳቸውን ያጠፉ ሰዎች ወይም ርኩሳን በሚቀበሩባቸው እና ከቅዱሳን መቃብር ቅጥር ግቢ ውጭ ባሉ ተራ በታዎች እንዲቀበሩ አወጁ።

በወቅቱ የአራጣ ብድር የተወገዘው በክርስትና እምነት ስለሆነ ጁዲዝም የአራጣ ብድርን አያወግዝም አይከለክልምም ነበር። ስለዚህ በወቅቱ አብዛኛዎቹ የባንክ አገልግሎት ሰጪዎች አይሁዶች ነበሩ። በነገራችን ላይ በወቅቱ በአራጣ አበዳሪነት እና በገንዘብ ምንዛሪ ስራ ላይ የተሰማሩት አብዛኛዎቹ አይሁዳውያን በመሆናቸው በሁለተኛው የአለም ጦርነት እና ከዚያም በፊት በአይሁዳውያን ላይ ያነጣጠረ ጥቃት Jewish pogroms መነሻ እንዲሆን ያደረገው በዚህ መልክ አራጣ የወሰዱ አይሁዳውያን ያልሆኑ ሰዎች ብድሮቻቸውን መክፈል ሲሳናቸው ያነሳሱት የበቀል እሳት እንደሆነ ይታመናል።

ይህንኑ ታሪካዊ ዳራ ተንተርሰን እስካሁን በስራ ላይ ያለውን አንጋፋውን እና ጥንታዊውን ባንክ ማወቅ ግድ አይለንም? እንዴታ! **"ይህ ጥንታዊ ባንክ የጣልያኑ 'ባንካ ሞንቴ ዴይ ፓስኪ ዲ ሲዬና'- Banca Monte dei Paschi di Siena ይባላል።"** ባንኩ ለአገልግሎት ክፍት የሆነውም ከዛሬ 546 ዓመት በፊት እ.ኤ.አ 1472 ዓ.ም ነው። ይሁን እንጂ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በእድሜ አንጋፋ ተብሎ ይታወቅ የነበረው እና እ.ኤ.አ. በ1466 ለአገልግሎት ክፍት የሆነው የስዊዘርላንዱ ዌግሊን ባንክ ኤንድ Wegelin & Co የተሰኘው ባንክ ቢሆንም እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 2013 ጀምሮ ስራውን በይፋ ሙሉ በሙሉ ያቋረጠ በመሆኑ ባንካ ሞንቴ ዴይ ፓስኪ ዲ ሲዬና እስከ ዛሬ ድረስ በስራ ላይ መሆኑ የአንጋፋነቱን ማዕረግ እንዲረከብ አድርጎታል።

> "ይህ ጥንታዊ ባንክ የጣልያኑ 'ባንካ ሞንቴ ዴይ ፓስኪ ዲ ሲዬና'- Banca Monte dei Paschi di Siena ይባላል።"

በሰሜናዊው የጣልያን ግዛት ባንኮች የላሞች ግብዓት የሆነውን ቺዝ በመያዣነት በማሰብ የአርብቶ አደሮች ብድር ለአርብቶ አደሮች ይሰጣሉ። በመያዣነት የቀረበው ቺዝ በባንኩ ኃላፊ አማካኝነት ከ2-3 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ በልዩ የማከማቻ እና ጥብቅ በሆነ ቦታ ለምግብነት ብቁ እስኪሆን ድረስ እንዲቀመጥ ይደረጋል። ተበዳሪው ቺዙ ለምግብነት ዝግጁ በሆነበት ጊዜ ውስጥ ብድሩን መመለስ ካልቻለ ባንኩ ቺዙን ለገበያ አቅርቦ የብድሩን ገንዘብ ያወራርዳል።

**"በዘመናዊው ስዊዘርላንድ በድምሩ 52 ትሪሊዬን የአሜሪካን ዶላር ተቀማጭ ገንዘብ ክምችት ያላቸው 400 ያህል ባንኮች አሉ።"** ከእነዚህ ባንኮች በአንዱ በቭላድሚር ኢሊይች ሌኒን ስም እ.ኤ.አ በ1902 በ13 ስዊስ ፍራንክ የተከፈተ የሂሳብ ቁጥር ዛሬም ድረስ ሳይዘጋ አለ።

በጊነስ የአለም ሪከርድ መመዝገቢያ መፅሃፍ በሚወጡ መረጃዎች ምን ያህል ይተማመናሉ? በዚህ መረጃ መሰረት በዓለማችን ከፍተኛ የባንክ ዝርፊያ የተደረገው በ1945 በጀርመኑ ራይክስ ባንክ Reichsbank ሲሆን ድርጊቱ ከፍተኛ የንብረት ዘረፋንም ሆነ የማሸሽ ተግባራትን ያካተተ ነበር። በዚህም በአሁኑ የግዢ ተመን ስሌት የ5 ቢሊዮን ዶላር ዋጋ ያላቸውን በባንኩ ውስጥ በናዚው ሰርድ ራይክ ባለቤትነት የተቀመጡትን አብዛኛውን የወርቅ ክምችት ጨምሮ ቀደም ሲል በናዚ አመራሮች ከሌሎች አውሮፓውያን ሃገራት በስርቆት የተሰበሰቡ ውድ የባሕል ቁሳቁሶችን ጨምሮ ተዘርፏል።

> "በዘመናዊው ስዊዘርላንድ በድምሩ 52 ትሪሊዬን የአሜሪካን ዶላር ተቀማጭ ገንዘብ ክምችት ያላቸው 400 ያህል ባንኮች አሉ።"

**ምንጭ፡** Financial & Banking Association of Euro-Asian Cooperation(https://www.fbacs.com/en/articles/interesting-facts-about-banks.html)

## እናስተዋውቅዎ....

........ከገጽ 8 የዞረል

እድገት ያለው በደጂታል ባንኪንግ አገልግሎት ዙሪያ ነው ብዬ አምናለው፡፡ ባንካችን ለደንበኞች በቅርንጫፍ ውስጥ በሰው ኃይል ተጠቅሞ የሚሰጠው አገልግሎት ደንበኛው በራሱ ጊዜ በማንኛውም ሰዓት ከየትኛውም ቦታ 24/7 የባንክ አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ ሠራተኛውን ለሌላ የቢዝነስና የማርኬቲንግ ሥራ ማሰማራት ይችላል፡፡ የባንካችን የኦኘሬሽናል ወጪውንም ይቀንሳል፤ እንዲሁም ከዲጂታል የባንክ አገልግሎት ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡ በተጨማሪም የደንበኞች አገልግሎት የተቀላጠፈ እንዲሆን ያግዛል፡፡ ይህ አገልግሎት መኖሩ ነባር ደንበኞች ወደ ሌላ ባንክ እንዳይሄዱ ከማድረጉም በላይ ሌሎች አዳዲስ ደንበኞች ወደ ባንካችን እንዲመጡ የሚያስችል ነው፡፡ ዲጂታል ባንኪንግ ለባንካችን ከሚሰጠው ጥቅም ባሻገር የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚ ያልሆኑ የማህበረሰብ ክፍል በደጂታል ባንኪንግ ተደራሽ ይሆናሉ፡፡ ነባር ደንበኞችም ቀላል፣ ቀልጣፋና ምቹ የሆነ የባንክ አገልግሎት 24/7 ሰዓት እንዲያገኙ ያስችላል፡፡

**ድምጸ ብርሃን፡** አገልግሎቶቹን በተለያዩ ጊዜያት ለማስተዋወቅ በነበረው ጉዞ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ምንድንናቸው?

**አቶ ፈዬራ፡** የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት በተፈለገው ፍጥነት ለማህበረሰቡ እንዳይደርስ የማህበረሰቡ ስለ ዲጂታል ባንክ ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆን በሥራችን ላይ እንቅፋት ሆኗል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ኘሮግራም በመቅረጽ ለባንካችን ሠራተኞች ተከታታይ ሥልጠናዎች በመስጠት ላይ እንገናኛለን፡፡ በዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት ያለው የማህበረሰቡ ግንዛቤ ደረጃ ከፍ እንዲል በተለያዩ ሚዲያዎች ማስታወቂያዎች እየተሰራጨ ይገኛሉ፡፡

**ድምጸ ብርሃን፡** እስቲ በመጨረሻም በቅርቡ ይፋ የሚደረጉ እና በዝግጅት ላይ ያሉ አገልግሎቶች ካሉ ቢገልጹልን?

**አቶ ፈዬራ፡** ባንካችን የደንበኞቹን ፍላጐት ይበልጥ ለማርካት በየጊዜው አዳዲስ የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎቶች እያቀረበ ይገኛል፡፡ በቅርቡም የተጓዦች የቪዛ ቅድመ ክፍያ ካርድና የነዳጅ የክፍያ አገልግሎት ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ በመሥራት ላይ እንገኛለን፡፡

**ድምጸ ብርሃን፡** ስለነበረን ቆይታ በድጋሚ ከልብ አመሰግናለው!

**አቶ ፈዬራ፡** እኔም አመሰግናለው!

# ተሞክሮ



በሃገራችን ተከስቶ በነበረው ጦርነት በአብዛኛው የሰሜኑ የአገራችን ክልል ያሉ የባንኩ ቅርንጫፎች ከፍተኛ በሚባል ደረጃ ጉዳት እና ውድመት እንደደረሰባቸው ይታወቃል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ኮንቦልቻ ከተማ ላይ በነበረው ጦርነት የብርሃን ባንክ የኮምቦልቻ ቅርንጫፍም የዚሁ ዝርፊያና ውድመት ሰለባ ሆኗል፡፡ ለአብነትም የቢሮ ጠረጴዛዎች፤ የበር እና የመስኮት መስታወቶች እና ካዝናውን በማውደም በካዝና ውስጥ የነበረው ገንዘብ ሊዘረፍ ችሏል፡፡

በዚህ ወቅት የደረሰው ጥፋት ከዚህ የከፋ እንዳይሆን በቅርንጫፉ ታታሪ የጥበቃ ሰራተኛ አቶ አንዱአለም ተሾመ አማካኝነት በርካታ ንብረቶች ሊተርፉ ችለዋል፡፡

የጥበቃ ሰራተኛው በወቅቱ ራሱን በመቀየር ሌላ ህንጻ ውስጥ እያደረ አንድ በአንድ የባንኩን ንብረቶች ማለትም 6 ኮምፒውተሮች ከእነ ሙሉ አክሰሰሪያቸው፤ የኔትወርክ ሞደም ሙሉ ዕቃዎች፤ ፎቶ ኮፒ ማሽን፤ 2 ፓስቡክና ኤችፒ ፕሪንተር፤ ስምንት ወንበሮች፤ ትልቁ የብር መቁጠሪያ ማሽን፤ የውጭ ምንዛሬ መለያ ማሽን፤ ስካነር፤ 2 የመስመር ስልክ ቀፎዎች እና ሌሎችንም ሊያተርፍ ችሏል፡፡

ይህ ጀግና ሰራተኛ በጦርነቱ ወቅት ባንኩን ለማትረፍ በጦር መሳሪያ ሰደፍ እስከ መመታት እራሱን መሰዋዕት በማድረግ ቅርንጫፉን ከሌሎች በጦርነቱ ከተጎዱ ቅርንጫፎች ቀድሞ ቶሎ ስራ በመጀመር ለደንበኞች አገልግሎት እንዲሰጥ ምክኒያት ሆኗል፡፡


በዚህም የደሴ፤ የመርሳ፤ የወልዲያ እና የቆቦ ከተማን ጨምሮ በአቅራቢያ እስከ 193ኪ.ሜ ርቀት ያሉ ደንበኞችን ጭምር ለማስተናገድ አስችሎታል፡፡

**Tel** +251 11 663 0127
+251 11 618 5732 / +251 11 662 9568
**Fax** +251 11 662 3431 **Swift** BERHETAA
**E-mail** info@berhanbanksc.com
**www**.berhanbanksc.com
**P.O.Box** 387 Code 1110 Addis Ababa, Ethiopia

ብርሃን Berhan Bank
እንደ ስማችን ብርሃን ነው ሥራችን!

# የበረራ ትኬት አገልግሎትን በቀላሉ ያግኙ

ከብርሃን ባንክ ጋር በአጋርነት እየሰሩ ከሚገኙት የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና ጉዞ ጎ የሞባይል ስልክ መተግበሪያ የበረራ ትኬቶችን በቀላሉ ይግዙ።



## የብርሃን ባንክ
## የበረራ ቲኬት ክፍያ አገልግሎት

ብርሃን ባንክ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ እና ከአስር አየር መንገዶች ጋር አብሮ ከሚሰራው ጉዞ ጎ ጋር በመሆን የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር የበረራ ትኬቶችን አቅርቦሎታል። ስለሆነም የበረራ ትኬት ክፍያዎን በሞባይል ባንኪንግ (*881#) በመደወል ወይም በብርሃን ባንክ የስልክ መተግበሪያ ወይም በኢንተርኔት ባንኪንግ (https://berhanonline.et) ወይም በአቅራቢያዎ በሚገኝ ቅርንጫፍ በመቅረብ መፈፀም ይችላሉ፡ ፡

Berhan Bank

እንደ ስማችን ብርሃን ነው ሥራችን!

ለበለጠ መረጃ
በ7473 የጉዞ ጎ የጥሪ ማዕከል
+251 11 650 7400 ይደውሉ


Tel +251 11 663 0127 / +251 11 618 5732
+251 11 650 7425
Fax +251 11 662 3431 Swift BERHETAA
E-mail info@berhanbanksc.com www.berhanbanksc.com
P.O.Box 387 Code 1110, Addis Ababa, Ethiopia


www.berhanbanksc.com

Experience

# Stress-free Banking

Fast Turnarounds | Bank online at your convenience

Bank comfortably through your phone | Access your funds 24/7



GET IT ON Google Play

berhanbanksc

www.berhanbanksc.com

ብርሃን
Berhan Bank

ለበለጠ መረጃ
+251 11 663 0127
+251 11 618 5732 ይደውሉ